# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ጥቅምት 10 ቀን 2005 ዓ.ም**

**የመለስን ተረት ለመድገም የሞከረው ኃይለማርያም ደሳለኝ ህዝቡን ሲያስፈራራ ተደመጠ፤**

**ከወያኔ ፓርላማ አባል ተቃውሞ ደረሰበት**

**የፌዴራል ፖሊስ አባሎች ስራ መልቀቃቸው የወያኔ ቡድን ባለስልጣናትን ክፉኛ አስደንግጦዋል ፤**

በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ የተሾመው የደቡቡ ተወላጅ ኃይለማርያም ደሳለኝ ማክሰኞ ጥቅምት 6 ቀን 2005 ዓ.ም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ከነባር የወያኔ ባለስልጣናት የተሰጠውን ትዕዛዝ ሲያነበንብ መዋሉ ታወቀ።

ከመለስ አቁዋም ጋር አንዳችም ለውጥ የሌለውና በነባር አመራሮች ትዕዛዝ የሚንቀሳቀሰው ይሄው ግለሰብ መስከረም 28 ቀን 2005 ዓ.ም ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ባደረጉት ንግግር ላይ መብራሪያ ለመስጠት ማክሰኞ ዕለት በምክር ቤት አዳራሽ ተገኝቶ በሰጠው ማብራሪያ አሁንም ወያኔ ከየትኛውም ሰላማዊ ቡድን ጋር አብሮ ለመስራት በጎ ፍቃድ እንደሌለውና በተለይ ለዲሞክራሲ የሚታገሉ ድርጅቶችንም ሆነ ግለሰቦችን እንደሚያሳድድ በይፋ በሚያመላክት መልኩ ተናግሮዋል።

ነባር የወያኔ ባለስልጣናት ከጀርባው ሆነው የሚመሩት እና የሚያንቀሳቅሱት ይሄው ግለሰብ ተፅፎ የተሰጠውን የሚያነበንብ....የተነገረውን የሚያስተጋባ..... የገደል ማሚቶ እንደሆነ እየተነገረለት ሲሆን ማክሰኞ ዕለት ባደረገው በዚሁ ማብራሪያ ላይ በሐይማኖት አባቶች እና በተቃዋሚ ፖለቲካ አመራሮች ላይም ዛቻ ሲሰነዝር ተደምጦዋል።

ኃይለማርያምን ከጀርባ ሆነው ከሚመሩት ከፍተኛ የወያኔ ባለስልጣን መሀከል አንዱና ዋነኛ ው በረከት ስምኦን እንዲሁም አዜብ መስፍን ባልተገኙበት የተደረገው ይሄው የምክር ቤት ስብሰባ ላይ ከሚከተለው የሐይማኖት እምነት በተጻራሪ መልኩ በተለይ በእስር ቤት በሚንገላቱ የፖለቲካ እስረኞች ላይ የከረር እና የመረረ አስተያየት ሲሰጥ እንደነበር ለማድመጥ ተችሎዋል።

በሀይማኖት ሽፋን እየተንቀሰቀሱ ህገ መንግስቱን ለመናድ የሚሩዋሩዋጡ ቡድኖችንም ሆነ ግለሰቦች በዝምታ አንመለከትም ያለው የወያኔው ተላላኪ ኃይለማርያም ደሳለኝ በሰላማዊ ፖለቲካ ትግሉ ውስጥ የሚሳተፉትንም በአሸባሪነት እየፈረጀ ማስፈራሪያ ሲሰጥም ተደምጦዋል።

የዚህን ግለሰብ ማብራሪያና ማስፈራሪያ ያደመጠው በምክር ቤቱ ብቸኛ የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካይ የሆነው አቶ ግርማ ሰይፉ ሀገሪቱ ሁለት አሀዝ አድገት እያስመዘገበች ነው የተባለውን በመቃወም ይህ የተባለው ቁጥር እድገት ቢኖር ኖሮ ሀዝቡ ለከፋ የኑሮ ውድነት አይዳረግም ነበር ስለሆነም የተሳሳተ እና ተጨባጭነት የሌለው ለፖለቲካ ፍጆታ ተብሎ የሚነገር ብቻ ነው በማለት የኃይማርያምን ገለፃ እያጣጣለ ተናግሮዋል ።

አቶ ግርማ አክሎም በአሁኑ ሰዓት የወያኔ ቡድን ከጎረቤት ሀገራት ጋር በሰላማዊ መንገድ እንሰራለን .....እየሰራንም ነው ... ከሻእቢያ ጋርም በሰላማዊ መንገድ ችግራችንን እንፈታለን እያለ ባለበት በአሁኑ ወቅት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ብሎም ለመልካም አስተዳደር ግንባታ ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ያሉትን የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች እና አባሎች በእስር እያንገላታና እያሰቃየ ነው ካለ በሁዋላ በተለይ በቅርቡ መሳሪያ መዝዘው በዜጎቻችን ላይ ጉዳት ያደረሱትን የሻእቢያ ወታደሮች በምህረት እየፈታ አንድም ነገር ባልተገኘባቸውና ለዲሞክራሲ የዘመሩትን እነ አንዱአለም አራጌና ጉዋደኞቹ አሸባሪዎች ብሎ መፈረጁ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን የሚያሳፍር ነው ብሎዋል።

የወያኔ የከሰረ ፖለቲካው የተጋለጠበት ይሄው ተላላኪ ግለሰብ በበኩሉ አንዳንዶች የሚጽፉትን እኛም እናነባለን እናም ሀገርን ለማፍረስ የሚደረግ ሙከራ ከመሆኑም ባሻገር የሽግግር ወቅት ይፈጠር ብለው የሚመኙና የሚጸልዩ ናቸው.......ይሁን እንጂ ሽግግር ብሎ ነገር የለም አሁንም ኢህአዴግ .....ወደፊትም ኢህአዴግ ብቻና ብቻ ነው ሀገሪቱን የሚመራው ሲል መናገሩም ተደምጦዋል።

በተያያዘ በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ የምንዛሬ እጥረት ተከስቶዋል እየተባለ በሰፊው እየተናፈሰ ይገኛል ይሄ ምን ያህል እውነት ነው ተብሎ ከወያኔ የምክር ቤት አባል ከሆነው አንድ ግለሰብ ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ አንዴ አለ ሌላ ግዜ የለም እያለ ሲያምታታና ሲያተራምስ እንደነበረም ተደምጦዋል።

ግራ የተጋባውና መያዣ መጨበጫ ያጣው ይሄው አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር አንዴ የውጭ ምንዛሪ እጥረት የለም አሉባልተኞች የሚያስወሩት ነው ሌላ ግዜ ደግሞ የመለስን መሞት ተከትሎ በተደረገው የአመራር ሽግግር ወቅት ጥቂት ባለሀብቶች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በመጠየቃቸው የተፈጠረ እጥረት ነው በማለት እርስ በርሱ የተጣረሰ ገለጻ ሲያደርግ እንደነበርም ለማድመጥ ተችሎዋል።

በሀገሪቱ ውስጥ በተለያዩ የንግድ ስራ ተሰማርተው የሚገኙ ባለሀብቶች የውጭ ምንዛሪ ብሔራዊ ባንክን ጭምር ጠይቀው አንዳችም ገንዘብ እንደሌለ ተነግሮዋቸው ስራ ካቆሙ ወራት የተቆጠረ መሆኑ እየታወቀ የውጭ ምንዛሪ እጥረት የለም አሉባልተኞች የሚያስወሩት ነው እያለ እንደ ሙዋቹ አለቃው መደንፋቱና ለማጭበርበር መሞከሩ ከወዲሁ ከፍተኛ ትዝብት ላይ እየጣለው መሆኑ ታውቆዋል።

ከቅርብ ግዜ ወዲህ በከፍተኛ ሁኔታ በማደግ ላይ ካሉ ሀገራት ጋር ወዳጅነት ፈጥረው በሀገሪቱ ህዝቦች ስም ብድር እያግበሰበሰ መሆኑን የተናገረው ይሄው ግለሰብ በተለይ ከቻይና..... ከቱርክ ...ከህንድ እና ከሌሎችም ሀገራት በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ብድር በማግኘታቸው የውጭ ምንዛሬ እጥረት የለም ብሎ ይለፍፍ እንጂ አሁንም ድረስ ችግሩ እንዳልተቀረፈ ባለሀብቶች በንዴት እየተናገሩ ይገኛሉ::

ሰሞኑን ኃይለማርያም በምክር ቤት ተገኝቶ ንግግር ባደረገበት ወቅት እንኳዋን አንዳችም የውጭ ምንዛሪ እንደሌለ የተናገሩት የብሔራዊ ባንክ ምንጮች ስሙ ባልታወቀ ከፍተኛ የህወሀት ባለስልጣን ትዕዛዝ በቅርቡ በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ለግዥ በሚል ከብሔራዊ ባንክ መውሰዱንም አጋልጠዋል::

የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች በበኩላቸው አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ከመለስ ጋር አንዳችም ልዩነት የሌለው ከጀርባ ሆነው በሚያሽከረክሩት ግለሰቦች የሚመራና የራሱ አካሔድ የሌለው ነው ሲሉ እየተቹት ይገኛሉ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ እሁድ ጥቅምት 4 ቀን 2005 ዓ.ም በአዲስ አበባ በተደረገው የአፍሪካ ዋንጫ የእግር ኳዋስ ውድድር ላይ በተከሰተ ብጥብጥ አንዲት ወጣት ስትገደል ሌሎች በርካታ ወጣቶች ለከፋ ጉዳት መዳረጋቸው ታወቀ::

በአዲስ አበባ ስታዲየም እሁድ ጥቅምት 4 ቀን 2005 ዓ.ም የኢትዮጵያ ብሔራዊ የእግር ኳዋስ ቡድን ከሱዳን አቻው ጋር ውድድር ባደረገበት ወቅት ጨዋታውን ለመመልከት መጥቶ የመግቢያ ትኬት አልቆበት በየአደባባዩ በተሰቀሉ ስክሪን ሲመለከት የነበረው ህዝብ በጥበቃ ላይ ከነበሩ የፌዴራል ፖሊሶች ጋር በመጋጨቱ በሁለቱም ወገን ከባድ ጉዳት መድረሱ ታውቆዋል::

አንዲት እድሜዋ 30ዎቹ ውስጥ የምትገኝ ወጣት ሴት በፌዴራል ፖሊስ ተደብድባ ስትገደል ቁጥራቸው የበዙ ወጣቶችም በሰደፍና በጀርመን ሰራሽ ዱላ ሴት ወንድ ሳይሉ ከባድ ድብደባ የተፈጸመባቸው ሲሆን ወጣቶቹም በእልህና በብስጭት በወሰዱት እርምጃ ከ8 ያላነሱ የፌዴራል ፖሊሶች ከባድ ጉዳት እንደደረሰባቸው ታውቆዋል::

የፌዴራል ፖሊሶች በወሰዱት ዘግናኝ የድብደባ እርምጃ ሔለን የተባለች አንዲት ወጣት ወዲያው ስትሞት ሌሎች ደግሞ ከባድ ድብደባ ደርሶባቸው በተለያዩ የግል ሐኪም ቤት የተወሰዱ ሲሆን 8 የፌዴራል ፖሊሶች በደረሰባቸው ድብደባም እራሳቸውን ስተው ወደ ፖሊስ ሆስፒታል እንደተወሰዱ ማረጋገጥ ተችሎዋል::

እግር ኳዋሱን ለመደገፍ አደባባይ የወጣው ህዝብ በፌዴራል ፖሊሶች አላስፈላጊ እንግልት እና ወከባ ስለደረሰበት በብስጭት የተነሳ ግጭት መሆኑን የገለጹት በስፍራው የነበሩ የአይን እማኞች በድብቅ በየግንቡ ስር ተቀምጠው የነበሩ የፌዴራል ፖሊሶች በወሰዱት እርምጃ ብዙ ሰው ከባድ ጉዳት እንደደረሰበትም ለማወቅ ተችሎዋል::

ለ31 ዓመታት ከአፍሪካ እግር ኳዋስ ተገልሎ የነበረው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን እድሉን ለማግኘት የመጨረሻ የማለፊያውን ጨዋታ ለማድረግ በአዲስ አበባ ስታዲየም የሱዳን አቻውን

በገጠመበት ወቅት የህዝብ ድጋፍ የሌላቸው በተለይ በአሁኑ ሰዓት ሀገሪቱን ከጆርባ ሆነው እያሽከረከሩ ናቸው የሚባሉት የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤው ካሳ ተክለብርሀን እና በረከት ስምኦን መገኘ ታቸው በታዳሚው ዘንድ ግራሞትን መፍጠሩ ታውቆዋል።

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከሞተ በሁዋላ ከፍተኛ ስልጣን በስውር እንደያዘ የሚነገርለት በረከት ስምኦን በብዙ ሺህዎች የሚቆጠር ህዝብ በተሰባሰበበት ይቅርና ጥቂት መቶዎች ባሉበት ሁሉ ብቅ ማለት የጀመረ መሆኑን የጠቆሙት የፖለቲካ ተንታኞች እሁድ ጥቅምት 4 ቀን 2005 ዓ.ም በአዲስ አበባ ስታዲየም በክብር እንግድነት የተገኘውን ካሣ ተክለብርሀንን ተከትሎ መምጣቱ ብዙዎችን ያስገረመ ጉዳይ ሆኖዋል።

የወያኔ ከፍተኛ ቁንጮ ባለስልጣናት በስታዲየሙ የተገኙት የኩዋስ ፍቅር እና የህዝብ ድጋፍ ኖሮዋቸው ሳይሆን የከሰረ ፖለቲካቸውን ለመጠገንና የህዝብ ድጋፍ ለማገኘት ሲሉ የፈጸሙት ተግባር መሆኑን የጠቆሙት እነዚሁ የፖለቲካ ተንታኞች በተለይ በረከት ስምኦንና ካሳ ተክለብርሀን በአብዛኛው ቦታዎች መገኘታቸው አስገራሚ ነው ብለዋል።

በዕለቱ የተደረገውን ጨዋታ ለመመልከት በስታዲየሙ ውስጥ ከገባው 30 ሺህ ተመልካች በተጨማሪ የመለስን የቀብር ስነ ስርዓት ለማስተላለፍ ሲሉ በከፍተኛ ወጪ በተለያዩ አደባባዮች በተከሉዋቸው ስክሪኖች ሲመለከት የነበረው ህዝብ ብሔራዊ ቡድኑ በማሸነፉ ከመደሰቱ የተነሳ የሚያደርገውን ያጣ ቢሆንም በየመሀሉ ግን የወያኔን ቡድን ሲያወግዝ መደመጡንም በስፍራው ከነበሩ እማኞች ለማረጋገጥ ተችሎዋል።

ኃይለማርያም ፌከኛው መሪያችን......ምን ግዜም አንዲት ኢትዮጵያ .....የታሰሩ ፖለቲከኞች ይፈቱ......ብሔራዊ እርቅ አሁኑኑ......የሚሉና የመሳሰሉት መፈክሮች ሲስተጋቡ እንደነበር እነዚሁ በስፍራው ከነበሩ ተመልካቾች ያገኘነው መረጃ ገልጾዋል።

ከሱዳን አቻው ጋር በመስከረም ወር መጀመሪያ ላይ በሱዳን ኡምዱርማን ስታዲየም ተጋጥሞ በዳኛ ተፅዕኖ 5 ለ 3 ተሸንፎ የመጣው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በደርሶ መልስ ጨዋታ በአዲስ አበባ ስታዲየም 2 ለ 0 በማሸነፉ በደቡብ አፍሪካ ለሚደረገው 29ኛው የአፍሪካ ዋናጫ ማለፉ መላው የኢትዮጵያን ህዝብ ያስደሰተ እንደነበር ታውቆዋል።

ከብዙ ድካምና ጥረት በሁዋላ የተገኘውን ድል የወያኔ ቡድን አመራሮች እነሱ ያመጡትና ያስገኙት በማስመሰል በየመድረኩ የፖለቲካ ድጋፍ ለማግኛ እየለፈፉ ቢሆንም ለድሉም ሆነ ለውጤቱ ማማር ትልቁን አስተዋኦ ያደረጉት ተጨዋቾቹና አሰልጣኞቹ ናቸው።

በመጨረሻም የወያኔ ስርዓት ዋነኛ ምሰሶ ናቸው ብለው ባለስልጣናቱ የሚመኩባቸው የፌዴራል ፖሊስ አባላት ከቅርብ ግዜ ወዲህ በከፍተኛ ሁኔታ ስራቸውን እየለቀቁ መሆኑ ታወቀ።

የወያኔ ቡድን የሚያራምደው ዘረኝነት ፖሊሲ ያስመረራቸው መኮንኖች እና የበታች ሹሞች እንዲሁም ሲቪል ሰራተኞች በየቀኑ እየለቀቁ ስራቸውን ትተው እንደሚቀሩ ከፌዴራል ፖሊስ አስተዳደር ክፍል ውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል።

በህክምና፤ በምርመራ፤ በጥበቃ፤ በሹፌርነት እና በሌሎች በተለያዩ የስራ መስኮች ላይ ተሰማርተው ሲሰሩ የነበሩ የፌዴራል፤ የማረሚያ ቤት እና የአዲስ አበባ ፖሊሶች ስራ እየለቀቁ በመሆኑ በወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ዘንድም ድንጋጤ መፍጠሩ ታውቆዋል።

የፖሊስ አባሎቹ ስራ መልቀቃቸው ክፉኛ ያስደነገጣቸው ከፍተኛ አመራሮች በየጣቢያውና በየማረፊያቸው ውስጥ አስቸኳዋይ ግምገማ ተብለው የፌዴራል ፖሊስ ...የማረሚያ ቤት ፖሊሶች እንዲሁም የአዲስ አበባ ፖሊሶችን ወጥረው የሰነበቱ ቢሆንም ሰራዊቱ አቋዋሙ አንድ እና አንድ በመሆኑ አሁንም ስራ እየለቀቁ ያሉት አባሎች ቁጥር ብዙ መሆናቸው ታውቆዋል።

አባሎቹን ለማቆየት ሲሉ የስራ መልቀቂያ የሚሰጣችሁ ጥያቄ ካቀረባችሁ ከአንድ ወር በሁዋላ ነው ቢባሉም መኮንኖቹም ሆኑ የበታች ሹሞቹ ከእንግዲህ እዚህ በዘረኝነት በተተበተበ ተቋዋም ውስጥ መስራት አንፈልግም በማለት ያለ መልቀቂያም እየወጡ እንደሆነ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።በሌላ በኩል የፌዴራል ፖሊስ አባሎች እየለቀቁ ባለበት በዚህ ግዜ ምንም የማያውቁና ያልተማሩትን ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እየመለመሉ በተለያዩ የጦር ካምፖች ውስጥ እያሰለጠኑ መሆኑንም ከፌዴራል ፖሊስ ውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል።